**ሳምንታዊ ዜና (ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ. ም.)**

**ወያኔ 800 የጐንደር ገበሬዎችን አፍሶ ሱዳን ውስጥ አሰረ፣ 1600 ኪሎ ሜትር መሬት ቆርሶ ለሱዳን ሰጠ፣ የኢትዮጵያ ገበሬዎችም ከመልካቸው ወንዝ ውሃ እንዳይቀዱ በሱዳን ወታደሮች ተከለከሉ፣ መለስ ከነጋዴዎች ጋር ባደረገው ስብሰባ ነጋዴዎቹ ሕልውናችን ምንድነው አሉ፣ ምላሽም ሳይሰጣቸው ተበተኑ፣ በሁርሶ 10 ሺህ ጦር አሁንም ተመረቀ »»»»»»»»»»»»»»**

**ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ ሌላም ዜና በዝርዝር ያንብቡ ...............**

የኢትዮጵያን መሬት ገምድሎ ለሱዳን ከሰጠ በኂላ አይኔን ግንባር ያድርገው አልሰጠሁም ገና በስምምነት ሂደት ላይ ነኝ በማለት ድርቅ ያለ ውሸት የዋሸው የወያኔ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መግለጫ አወጣ::

ከ70 ሺህ በላይ ንጹህ ኢትዮጵያውያንን ለሞት የዳረገበት ባድመን የአለም አቀፉ ፍርድ ቤት ለኔ የወሰነለኝ በመሆኑ የደስታ ሰልፍ አደባባይ ውጡ በማለት የውሸት ጡሩንባቸውን የነፋት የወያኔው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስዩም መስፍንና ቡድኑ አሁን ደግሞ ለሱዳን መሬት ቆርሰው ከሸጡ በኂላ የጐንደር ሕዝብ ሲያመፅ ሕዝብንና መንግስትን ለማጋጨት አንዳንድ ግለሰቦችና መገናኛ ብዙሃኖች እያሴሩብኝ ነው በማለት የአዞ እንባውን ሲያፈስ ተስተውሏል::

በአሁን ሰዓት ግን ወያኔ ከኢትዮጵያ መሬት ላይ ቆርሶ ለሱዳን በመስጠቱ በአካባቢው ከፍተኛ የሕዝብ ቁጣ ተቀስቅሶ እንደሚገኝ ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልጿል::

በደረሰን ዘገባ መሠረት ከሁመራ እስከ ጋምቤላ ድረስ በአጠቃላይ 1600 ኪሎ ሜትር ርቀት ሲኖረው፣ በጐንደር በኩል ደግሞ ከደሎላ እስከ ነፍስ ገቤ ተብሎ እስከሚጠራው አካባቢ 600 ኪሎ ሜትር ርቀት እንዳለውና ከነፍስ ገቤ እስከ ጋምቤላ ድረስ ደግሞ 1000 ኪሎ ሜትር ርቀት መኖሩን የገለጸው ዘገባ በጋምቤላ በኩል 36 ኪሎ ሜትርና በሁመራ በኩልም በተመሳሳይ 25 ኪሎ ሜትር በአጠቃላይ 61 ኪሎ ሜትር ለሱዳን መስጠቱን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ያብራራል::

የወያኔ ሸርክ የሆነው የአልበሽር መንግስት ወታደሮቹን ወደዚሁ ስፍራ ከጥቂት ወራት በፊት አስገብቶ አስፍሮ የምሽግ ግንባታ እና ካምፖችን ሰርቶ እንቅስቃሴ ያደርግ የነበረ ቢሆንም በጐንደር ውስጥ ደሎላ ተብሎ የሚጠራው አካባቢ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያኖች በሱዳን ወታደሮች ላይ ጥቃት ሰንዝረው መኮንኖችን ጨምሮ 20 ወታደሮችን የገደሉ ሲሆን 2 ወታደራዊ ካምፖችን አቃጥለው ከአካባቢው ያባረሯቸው መሆኑን ይኸው የደረሰን ዘገባ ገልጿል::

ይህ እርምጃ የተወሰደበት የሱዳን መንግስት በሜካናይዝድ የተጠናከረ ጦር ወደ ኢትዮጵያ ድንበር በማስገባት ጥቃት አድርሰውብኛል ባላቸው በደሎላ አካባቢ ነዋሪዎች ላይ የአፀፋ እርምጃ በመውሰድ፣ በማፈናቀልና የግል አንቨስተሮች ንብረትን በማውደምና በመዝረፍ ወንጀል የፈጸመ ሲሆን ወያኔ ግን አበጀህ እያለ ከማጨብጨብ ባለፈ አንዳችም እርምጃ ካለመውሰዱም በተጨማሪ ለሀገሪቱ ዜጐች ተቆርቁሮ ያደረገው እንደሌለ ይኸው ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አጋልጧል::

አይን አውጣውና ልበ ድፍኑ ወያኔ በዜጐች ላይ የሱዳን መንግስት ሰብአዊ ጥሰትና ውድመት ሲፈፀምባቸው ዝም ከማለቱም በላይ በጋምቤላ በኩል 36 ኪሎ ሜትር በሁመራ

በኩል ደግሞ 25 ኪሎ ሜትር ለሱዳን ማስረከቡን ያረጋገጠው የጐንደር ሕዝብ የጐበዝ አለቃ እየመረጠ ለፍልሚያ ዝግጁ መሆኑን የገለጸው ይሄው ዘገባ «ከእንግዲህ ወዲያ ወያኔም ቢሆን ለሱዳን ተደርቦ ይምጣ እንጂ ለረጅም ዘመናት ከቅድመ አያቶቻችን በፊት የነበረ እኛም ልጆቻችንም እዚሁ እትብታችን የተቀበረበትን ለሱዳን የተሰጠውን መሬት እስኪመለስ ድረስ ትግላችን ይቀጥላል» በማለት ሕዝቡ እየተጠራራ መሆኑን ይኸው ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልጿል።

አንድ የአካባቢው ተወላጅ የእድሜ ባለፀጋ እንደገለፁት ከሆነ የካቲት 3 ቀን 2000 ዓ.ም የወያኔና የሱዳን ጥምር ልዑካን ቡድን በታች አርማጭሆ ውስጥ ደሎላ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በሌሊት ሕዝብ ባልተገኘበት ሰዓት የድንበር ማካለያ (መለያ) ምልክት ሲተክሉ በአካባቢው ተወላጅ የሆነ አንድ ገበሬ ድርጊቱን በመመልከቱ በታጠቀው መሣሪያ ተኩሶ ቡድኑን ከአካባቢው ካባረረ በኋላ ሕዝቡን በመቀስቀስ ድንበር መለያ ብለው ያስቀመጡትን መልክት አፈርራሰው የጣሉት መሆኑን ያስታሰው ይሄው ዘገባ ወያኔ ከጐንደር ቆርሶ ለትግራይ የሰጠው መሬት ላይ አብደራፊ እና አብርሃ ጅራ ቀበሌዎች ውስጥ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በመንገሩ የአካባቢው ሕዝብ በቁጣና በንዴት ትጥቅ ትግል እንገባለን በማለት ከፍተኛ ተቃውሞ ሲያሰሙ እንደነበረም አብራርቷል።

ለዘመናት ተከብሮ የኖረውን የሀገሪቱ ዳር ድንበር ወያኔ በገንዘብና በጥቅም በመደለል ዙሪያውን እየቆረሰ እየሰጠ ሲሆን፣ የሕዝብን ሀብትና ንብረት ለ17 ዓመታት የዘረፈው አልበቃ ብሎት ዛሬ እንደገና የኢትዮጵያን መሬት ሸጦ ገንዘብ ለመሰብሰብ እየተሯሯጠ ከመሆኑም ባሻገር ወያኔ ተቃዋሚ ታጣቂ ኃይሎች ይንቀሳቀሱበታል ብሎ በመስጋቱ ጭምር ከጥቃት ያድነኛል በሚል ለዘመናት የኢትዮጵያ ግዛት የሆነውን ድንበር ቆርሶ መስጠቱ አሳፋሪና ወራዳ ተግባር መሆኑን የሀገሪቱ ሕዝቦች በቁጭትና በእልህ እየገለፁ ይገኛሉ።

የወያኔው ቡድን የአካባቢውን ሕዝብ ለማሳመን በቅርቡ አንድ ቡድን አዋቅሮ የነበረ ሲሆን፣ ይኸው ቡድን ወደ አካባቢው ተጉዞ «ጉዳዩን በሽምግልና እንጨርሰዋለን ተረጋጉ» በማለት ለማሞኘት ቢከጅልም የአካባቢው ሕዝብ ግን በመሬታችን በድንበራችን ሽምግልና የሚባል አናውቅም እስከመጨረሻው እንፋለማለን በማለት ቡድኑን ከአካባቢው ያባረሩ መሆኑን ዘገባው ገልጿል።

የድንበር መለያ የተሰጠው የካቲት 3 ቀን 2000 ዓ.ም መሆኑን የገለጸው ይሄው የደረሰን ዘገባ ይህንኑ ተከትሎ የተነሣውን የሕዝብ አመፅ ለመግታት በአዲስ አበባ ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም ምርጫን ተከትሎ የተቀሰቀሰውን የሕዝብ ተቃውሞ ለመበተን በጥይት ከ200 በላይ ንፁሃን ዜጐችን የገደለውን አግአዚ ጦር ከመጋቢት 6 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ወያኔ ይህንኑ አረመኔ በሕዝብ የተጠላ ጦር የሱዳን ወታደሮች ቦታውን እስኪይዙ ድረስ እንዲጠብቅ ተደርጐ በሁመራ አብደራፊ፣ በመተማ አቅራቢያ ሽንፋ በተባለ ቦታ የሰፈረ ሲሆን ከጦሩ በተጨማሪም ወያኔ በርካታ ቁጥር ያላቸው ካድሬዎቹን ከሁመራ እስከ ቋራ ድረስ ባሉ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ አስርጐ ያስቀመጣቸው ከመሆኑም በላይ «መንግስት የወሰደውን እርምጃ የሚቃወም ካለ ከፍተኛ ቅጣት ይጣልበታል» በማለት ሕዝቡን እያስፈራሩ መሆናቸውን የገለፀው ዘገባ ሕዝቡ ግን ከእንግዲህ ቋንቋችን አንድና አንድ ነው መሬታችን ለሱዳን አይሰጥም በማለት ከፍተኛ ቁጣ እየሰነዘረ እንደሚገኝም ዘገባው አብራርቷል።

የአካባቢው ሕዝብም «እትብታችን ለተቀበረበት ምድር፣ ለሀገራችን መሬት፣ ለዳር ድንበራችን መከበር እንፋለማለን በዚህ ምክንያት ከሱዳንም ሆነ ከወያኔ በኩል ለሚሰነዘርብን ጥቃትና ጭፍጨፋ አንበረከክም የመጣውን ሁሉ እንቀበላለን» በማለት ከፍተኛ ተቃውሞ እያሰሙ ሲሆን በየቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ተሰግስገው የነበሩ ካድሬዎች ከየተመደቡበት ቀበሌ ገበሬ ማህበር እየወጡ ወደ የወረዳዎቹ ከተሞች እየሸሹ መሆኑንም ዘገባው ጨምሮ ገልጿል።

በአሁን ወቅት የወያኔው ቡድን ከመጋቢት 6 ቀን 2000 ዓ.ም በአካባቢው አስፍሮት የነበረውን የአግአዚ ጦር አስወጥቶ በምትኩ የሱዳን መንግስት በሜካናይዝድ የተጠናከረ ጦር ያስፈረ ሲሆን፤ይህንኑ ወያኔና የሱዳን መንግስት በምስጢር ስምምነት ላይ ደርሰው መሆኑን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልፆ በአሁኑ ሰዓት ሽንፋንና አካባቢውን የሱዳን ጦር ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሮት እንዳለም አብራርቷል።

የሱዳን ጦር የሰፈረበትን ለም የኢትዮጵያ መሬት ተቆጣጥሮ ከመያዙም በተጨማሪ ኢትዮጵያውያኖችን ከሽንፋ ወንዝ ውሃ እንዳይቀዱና ከብቶቻቸውን እንዳያስግጡ የከለከለ ሲሆን በዚህም የተነሳ ሕዝቡ የጉበዝ አለቃ መርጦ ዱር ቤቴ እያለ መሆኑንም ዘገባው አስረድቷል።

ወያኔ በጥቅም የታወረ በመሆኑ ለሱዳን መሬት ከመስጠቱም ባሻገር ይህንን ድርጊት ያደናቅፋሉ ብሎ ያላቸውን ከ800 በላይ ኢትዮጵያውያን ገበሬዎችን ለቅሞ ወደ ሱድን ወስዶ በወታደራዊ ካምፕ ውስጥ ያሰራቸው ከመሆኑም በላይ በሜካናይዝድ የተጠናከረ የሱዳን ጦር በአካባቢው ከሰፈረው በተጨማሪ የወያኔ ጦርም በተመሳሳይ ወደ አካባቢው እያመራ መሆኑን ከአይን እማኞች የተገኘው ዘገባ ያስረዳል።

የሱዳን ጦር ከወያኔ ባገኘው ድጋፍ የተነሳ ሚያዝያ 30 ቀን 2000 ዓ.ም በጐንደር ታች አርማጭሆ ወረዳ ዱሳን ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ሠራዊት አስገብቶ ከአብዱራፊ ከተማ ወጣ ብሎ በስተምዕራብ በኩል ከገላ እሉባን እና ጓንግ ወንዝ መካከል የሚገኘውን የአንድ ኢትዮጵያዊ ኢንቨስተር የእርሻ ልማት በመዝረፍና በማቃጠል 24 ሠራተኞችን አፍነው ወስደው ሱዳን ውስጥ አስረዋቸው ይገኛሉ ያለው ዘገባ ከዚህም በተጨማሪ ለብዙ አመታት በውጭ ሀገር ሰርተው አጠራቅመው በእርሻ ልማቱ ስራ ላይ ተሰማርተው የነበሩ ኢትዮጵያውያንን አፍሰው በሱዳን የጦር ካምፕ ውስጥ አስረዋቸው እንደሚገኙም ይሄው ዘገባ አብራርቱዋል።

የወያኔ ባለሥልጣናት በድንበሩ አካባቢ ትልልቅ የእርሻ ልማት ያላቸውን ባለሀብት ኢትዮጵያውያንን በምስጢር በመሰብሰብ የኢትዮጵያን ጥቅም በሚጐዳ ሁኔታ ከሱዳን ጋር ድንበሩን ለማካለል እንዲቻል በማለት ሱዳን ርዕሰ ከተማ ካርቱም ድረስ ወስደው በማያውቁት ቋንቋ በአረብኛ በተዘጋጀ ሰነድ ላይ በግዴታ እንዲፈርሙ አድርገው የእርሻ ቦታዎችን ለሱዳን መንግስት የተሰጠባቸው ሲሆን ይህንኑ ተከትሎ አቤቱታ ቢያቀርቡም ወድዳችሁ የፈረማችሁት በመሆኑ አይመለከተንም በማለት ወያኔ እንዳባረራቸውና ለከፍተኛ ኪሣራ እንደተዳረጉ ሲገልጹ ተደምጠዋል። ሱዳን በአሁኑ ጊዜ ይህንን እርምጃ ልትወስድ የቻለችው በአባይ ወንዝ ላይ ብቻ የተመሰረተው ልማት ወደፊት አስተማማኝ ስላልሆነ ከኢትዮጵያ ለም መሬት ቆርሶ በመውሰድ የመንግስት እርሻን አስፋፍቶ ለመያዝ መሆኑንም ምንጮች ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል በጐንደር ውስጥ በሕዝቡና በሱዳን ጦር መካከል የተጀመረው ከፍተኛ ችግር ለወያኔ ስርዓት አደጋ በመሆኑ ስዩም መስፍን የመለስ ዜናዊን መልዕክት ይዞ ማክሰኞ ግንቦት 4 ቀን 2000 ዓ.ም ወደ ሱዳን ማቅናቱ ታውቋል፡፡

የወያኔው በድን ግራ ገብቶት አንዴ የወጣት ተወካይ ናቸው የተባሉ የፎረም አባላትን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ የሴቶች ተወካይ ናቸው የተባሉ የወያኔ አባሎችንና ሌሎችንም ሰብስቦ አነጋግሮ የነበረ ቢሆንም ያለ አንዳች ውጤት እርስ በእርስ ሲሞከሻሹ እየዋሉ የሕዝብ ሀብት እያባከኑ የሰነበቱ ሲሆን፤ ሰሞኑንም በተመሳሳይ መልኩ ከነጋዴዎች ጋር ውይይት ማድረጉ ታወቀ፡፡

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ሰሞኑን ከነጋዴዎች ጋር ሚሊኒየም አዳራሽ በተባለው መሰብሰቢያ ውስጥ ስብሰባ ያደረገ ሲሆን ከጥቂት ሆድ አደር የፓርቲ አባል ነጋዴዎች በስተቀር ብዙዎቹ በወቅታዊ ሁኔታ ላይ የሚያተኩር ጥያቄ አቅርበው ምላሽ ሳያገኙ መቅረታቸው ታውቋል፡፡

መለስ እንደለመደው ተሞካሽቼ እወጣለሁ ብሎ አስቦ የነበረ ቢሆንም የንግዱ ማህበረሰብ ባነሱዋቸው ፈታኝ ጥያቄዎች የተነሳ በንዴትና በብስጭት ጦዞ ለተጠየቀው ጥያቄ አንዳችም ምላሽ ሳይሰጥ አድበስብሶ ያለፈ መሆኑን የገለፁት የስብሰባው ተሣታፊ ነጋዴዎች አሁን ባለው ሁኔታ ጥቂት ከቀጠለ ወያኔ ሀገሪቷንና ሕዝቡዋን ምድረ በዳ አድርጐ ሊሰደድ እንደሚችል ከመለስ ተስፋ መቁረጥ አንጻር መረዳት ተችሏል ብለዋል፡፡

ብዙው ነጋዴ በአሁን ሰዓት በሐገሪቱ ውስጥ የንግድ ስራ ሞቷል በሚባልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል ምን እርምጃ ለመውሰድ አስባችኋል? መብራት በመጥፋቱ ሐገሪቷ ማግኘት የሚገባትን ገቢ ከማጣቷም በላይ በርካታ ፋብሪካዎች ከስራ ውጭ ሊሆኑ እየተቃረቡ ነው ለዚህስ ምን መፍትሄ ተዘጋጅቷል? አሁን ያለው ሁኔታ በአጠቃላይ ከእኛ ከነጋዴዎች አቅም በላይ በመሆኑ ምን ድጋፍ ሊደረግልን ታስቧል? የሚሉና ሌሎችንም ጥያቄዎች የተዥጐደጐዱለት ቢሆንም የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ አንድም የረባ ምላሽ ሳይሰጥ ይባስ ብሎ እንደደርግ ስርዓት ሁሉ ነጋዴውን ሲያስፈራራ መዋሉንም እነዚሁ ተሳታፊ ነጋዴዎች በአግራሞት ገልፀዋል፡፡

በተለይ አሁን በሀገሪቱ የተከሰተው የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት የናንተ የነጋዴዎች ኃላፊነት ነው በማለት እያስፈራራ የገለፀው መለስ ዜናዊ ነጋዴዎች የጠየቁትን አንድም ምላሽ ሳይሰጥ ግዴታቸውን ብቻ አሽክሞ በቁጣ ጀምሮ በማስፈራራት ያጠናቀቀው ስብሰባ መሆኑንም ገልፀዋል፡፡

እንደ ሌሎቹ ስብስባዎች አሞካሽተውና ሸልመው ያሰናብቱኛል ብሎ የገባው መለስ ይህ ሁሉ ቀርቶ ያልጠበቀውና ያላሰበው ጠጣር ጥያቄዎችን በማንሳታቸው በመበሳጨት እንደ ቀድሞው ሁሉ በመድረክ ላይ ሳይቦርቅ ባዶ ጩኸቱን ሲያቅራራ የዋለ መሆኑን የገለፁት እነኚሁ ነጋዴዎች መጨረሻ ላይ ማሳረጊያ አድርጐ የነጋዴውን ሀሳብ ለመቀየር ሲል ብቻ የኤርትራ መንግስት ጅቡቲን ለመውረር ያሰበው ሆን ብሎ የኛን ወደብ ተጠቃሚነት ለማሳሳት ነው በማለት የወተወተ ቢሆንም በነጋዴው ማህበረሰብ ዘንድ ስሜት ውስጣቸው ሊያጭር እንዳልቻለም አብራርተዋል፡፡

ወያኔ የራሱን የንግድ ማዕከሎች በየቦታው ከፍቶ እያስፋፋ ሕጋዊ ነጋዴዎችን አንገት አስደፍቶ እንደጋሪ ፈረስ ለጉሞ ለመንዳት ካለው ሕልም የመነጨ በርካታ ሙከራዎችን ያደረገ ቢሆንም ነጋዴው ሕብረተሰብ በትምህርት የታገዘ ስራ በመስራቱ በዚህ ያልተበገረለት መሆኑን የተረዳው ወያኔ በግዳጅ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ ደጋፊነትና አባልነት እያሳበበ አፍሶ ወደ እስር ቤት እያጐረ መሆኑን ከዚህ ቀደም ደጋግመን የዘገብን ሲሆን አሁንም በዚሁ ተግባሩ እንደቀጠለበት ከታሣሪ ቤተሰቦች የተገኘው ጥቆማ ያስረዳል።

በስብሰባና በተረት ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት የወያኔ ባለሥልጣናት ሕዝቡንና ሐገሪቱን ከአቅማቸው በላይ ግጠው ያካበቱትን ሀብት መሸሸጊያ አጥተው እየተጨነቁ ባለበት ወቅት 3ኛ የሩብ አመት ስብሰባ አደረግን ብለው ማወጃቸው ተሰምቷል።

ለሶስት ቀናት በተደረገው በዚሁ የወያኔ ስራ አስፈፃሚ ስብሰባ ላይ በአሁን ሰዓት በሀገሪቱ ስላለው የኑሮ ውድነትና ተዛማጅ የህዝቡ ችግሮች ዙሪያ አንዳችም ሐሳብ ያላነሱ መሆኑን የገለፁት ምንጮች ለእድሜያቸው ማስረዘሚያ በሚሆኑ አጀንዳዎች ዙሪያ ብቻ ሲወያዩ እርስ በእርሳቸው ሲሞከሻሹ እንደሰነበቱ ምንጮቹ ገልፀዋል።

አርብ ግንቦት 1 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ እስከ እሁድ ግንቦት 3 ቀን 2000 ዓ.ም ለ3 ቀናት ድረስ የወያኔ ስራ አስፈፃሚዎች የተባሉት ቱባ ቱባ ባለሥልጣናት የሕዝቡን ዋነኛ አጀንዳ ሳያነሱ በራሳቸው የስልጣን እድሜ ማራዘሚያ ናቸው በተባሉ በመከላከያ፣ በሻዕቢያ ዙሪያ እና በወታደራዊ ድጋፍ በኩል ምን ሊደረግ እንደሚገባው ብቻ ተወያይተው የቁዋጩ መሆኑን ምንጮቹ አጋልጠዋል።

በሀገሪቱ ዙሪያ እንደብራና የተወጠረው ወያኔ በዚህ ከፍተኛ ስጋት የገባው በመሆኑ ከሁለት ቀን ተኩል በላይ የተወያየ ሲሆን፣ በሻዕቢያና በሌሎችም ተቃሚዎች ዙሪያ እንዲሁ ሐሳብ አንስተው እንደተወያዩ የገለፁት ምንጮች በተለይ ከሱዳን ጋር ተስማምተው መሬት የሸጡበትን ሁኔታ በዝርዝር ከተነጋገሩ በኋላ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መግለጫ እንዲያወጣ ተስማምተው መወሰናቸውንም አጋልጠዋል።

በጅቡቲ በኩል የሻዕቢያ ቡድን ጥቃት ሊሰነዝር ያሰበው የእኛን ሕልውና ጥያቄ ውስጥ ለመክተት ነው በማለት መለስ ዜናዊ ለሹማምንቱ ያቀረበው ሐሳብ ተቀባይነት አግኝቶ ግዙፍ ጦር ወደ ስፍራው እንዲገባ መወሰኑን የገለፁት ምንጮች ውሣኔው በተላለፈ ጥቂት ሰዓታት ውስጥ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ሱዳንን አስመልክቶ መግለጫ ያወጣ ሲሆን፣ በጅቡቲ በኩልም ግዙፍ የጦር ኃይል እንዲሰፍር በተወሰነው መሠረት ተፈፃሚ መሆኑን ምንጮቻችን ገልፀዋል። ወያኔ ለራሱ እድሜ ማራዘሚያ የሚሆኑ እርምጃዎችን ወሰደ እንጂ ሕዝቡ የሚቀምሰው የሚልሰው አጥቶ በከፍተኛ የኑሮ ወድነት ውስጥ መኖሩን እያወቁ በሐገሪቱ አንዳችም ችግር እንዳልተፈጠረ አስመስለው እርስ በእርስ ሲያውካኩ መዋላቸው የሚያሳዝን ነው ያሉት ምንጮቹ ዛሬ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የአንድ ኩንታል ሩዝ ዋጋ 2000 ብር እያናጠረ የአንድ ኩንታል ጤፍ ዋጋ 1200 መሆኑን እያወቁ በሐሳብ ደረጃ እንኳዋን አለማንሳታቸው የወያኔ

ሹማምንት ሕዝቡ ላይ እየፈፀሙት ያለው ግፍና በደል ገና እንዳልተቋጨ የሚያሳይ ነው በማለት አጋልጠዋል።

ወያኔ ባደረበት ውስጣዊ ፍራቻ ሕዝቡን በረሀብና በችግር የስንግ ወጥሮ የራሱን እድሜ ለማራዘም ሲል ብቻ በየጊዜው ወታደሮችን እያሰለጠነ ከምስራቅ አፍሪካ በወታደራዊ ኃይል የበላይ ለመሆን ባቀደው መሠረት እየሰራ መሆኑን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ።

እንደምንጮቹ ገለፃ ከሆነ ሐገሪቷ ከምትችለው በላይ ከፍተኛ ወጪ እየተደረገበት ያለው ይኸው ወታደራዊ ተቋም መሆኑን ገልፀው ሰሞኑንም ይባስ ብሎ 10 ሺህ ወታደሮችን አሰልፎ ማስመረቁን በይፋ ገልጿል።

አንድ ወታደር ትጥቁንና ቀለቡን ጨምሮ በአንድ ወር ብቻ በሺህዎች የሚቆጠር ገንዘብ ወጪ እንደሚደረግለት ግልፅ የወጣ ነው ያሉት ምንጮች በአሁን ሰዓት ወያኔ ከ350- 400ሺህ ሠራዊት ያለው ሲሆን በየወሩ በቢሊዮን የሚቆጠር ብር ወጪ እያደረገ ሕዝብን ለረሀብና ለስቃይ መዳረጉ አሳፋሪና አሳዛኝ መሆኑን ገልፀዋል።

በአሁን ወቅት በመላው ሐገሪቱ ዙሪያ የታጣቂ ተቃዋሚ ኃይሎች እየተንቀሳቀሱ ግራ እያጋቡት ሲሆን ተጨማሪ ደግሞ በሱዳን ድንበር ዙሪያ እራሱ በፈጠረው ስግብግብነት ሌላ ግጭት ውስጥ በመግባቱ ሠራዊቱን እንደ ጨው በትኖ ያለበት ወቅት መሆኑን የገለፁት ምንጮች በዚህ የተነሳም ስጋት የገባው የወያኔ ቡድን ቅዳሜ ግንቦት 2 ቀን 2000 ዓ.ም በሁርሶ 10 ሺህ ጦር አሰልጥኖ ማስመረቁንም አጋልጠዋል።

የምስራቅ ዕዝ አዛዥ ሜ/ጄ/ል አብርሃ ወ/ማሪያም የሕወሓቱ ጄኔራል የመረቀው ጦር 6 ሺህ ነው ተብሎ የተገለፀ ቢሆንም በዕለቱ የተመረቀው ሠራዊት ብዛት ግን 10 ሺህ መሆኑን አጋልጠው፣ በቀጣይም በተቀሩት ማሰልጠኛዎች ውስጥ የሰለጠኑት ሌሎችም በቅርቡ ይመረቃሉ ሲሉ ምንጮች ገልፀዋል።

በምስራቅ፣ በደቡብ፣ ምስራቅ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን፣ ተወጥሮ ያለው ወያኔ አሁንም መፍትሄ ነው ብሎ የሚያስበው ወታደሩን ቁጥር ከፍ በማድረግ በመሆኑ አሁንም በርካታ ምልምል ወታደሮችን ማሰልጠኛ አስገብቶ እያሰለጠነ መሆኑን ምንጮች አጋልጠዋል።